ኢሕማልድ
JeCCDO

# JERUSALEM NEWSLETTER
# ዜና ኢየሩሳሌም

Volume 7 Issue 21
ቅጽ 7 ቁጥር 21

April, 2011 - June, 2011
ሚያዝያ 2003 - ሰኔ 2003

## Inside This Issue

## በዚህ ዕትም ውስጥ


| Inside This Issue | Page | በዚህ ዕትም ውስጥ |
|---|---|---|
| **NEWS** | | **ዜና** |
| Education Bureau grants books to JeCCDO | 1 | የትምህርት ቢሮው ለኢሕማልድ መጻሕፍት ለገሠ |
| JeCCDO signs agreement for water supply, sanitation, hygiene promotion project | 2 | የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጂን ፕሮጀክት ስምምነት ተፈረመ |
| JeCCDO participates in Go Green Afrique Africa International Fair | 3 | ኢሕማልድ ዓለም-አቀፍ ዐውደ-ርዕይ ላይ ተሳተፈ |
| Project to benefit more than 16,000 student | 4 | ከ16,000 በላይ ተማሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ተከፈተ |
| JeCCDO signs memorandum of understanding with Amhara Cluster Edukans Partners | 5 | ኢሕማልድ የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ |
| Community based organizations takeover projects of nearly 9 million birr | 6 | የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት 9 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ፕሮጀክት ከኢሕማልድ ተረከቡ |
| Comic Relief's Chief Executive Officer visits JeCCDO | 7 | የኮሚክ ሪሊፍ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ኢሕማልድን ጎበኙ |
| Grant award to reach children, guardians at risk of HIV and AIDS | 8 | ለኤች አይ ቪ እና ኤድስ የተጋለጡ ሕጻናትንና አሳዳጊዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገንዘብ ድጋፍ ተደረገ |
| Association supports orphan, vulnerable children | 9 | ማኅበሩ ወላጆቻቸውን ላጡና ለችግር ለተጋለጡ ሕጻናት ድጋፍ አደረገ |
| Society wins the National Hygiene and Sanitation award | 10 | ማኅበሩ አገር-አቀፍ የሥነ-ንፅህና ሽልማት አሸነፈ |
| **TRAININGS AND WORKSHOPS** | | **ሥልጠናና ዐውደ-ጥናት** |
| Project review, familiarization sessions take place | 11 | የፕሮጀክት ትግበራ፣ ውጤትና ማስተዋወቂያ ዐውደ-ጥናቶች ተካሄዱ |
| Key stakeholders workshop on Self Help Group Approach | 12 | በራስ አገዝ ቡድን ላይ ያተኮረ ዐውደ-ጥናት ተካሄደ |
| Workshop emphasizes urban agriculture's contribution to poverty reduction, environment | 12 | የከተማ ግብርና ለድህነት ቅነሳና ለአካባቢ ጥበቃ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተገለጸ |
| Workshop validates research findings | 14 | የዐውደ-ጥናቱ ተሳታፊዎች ለጥናቱ ውጤት ተቀባይነት ሰጡ |
| Workshop on gender sensitive modules | 14 | ሥርዓተ-ፆታን ያማከሉ መመሪያዎችን ለማዘጋጀት የምክክር ዐውደ-ጥናት ተካሄደ |
| Child parliament speaker visits the Netherlands | 16 | የሕጻናት ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ኔዘርላንድን ጎበኘ |
| Capacity development trainings to partner community based organizations' executives | 17 | ለአጋር የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት አመራር አካላት የአቅም ልማት ሥልጠናዎች ተሰጡ |
| Stakeholders' annual review meeting | 17 | የባለድርሻ አካላት ዓመታዊ ስብሰባ ተካሄደ |
| Trainees confirm to produce effective stories | 18 | ሠልጣኞቹ አመርቂ ታሪኮችን ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው ክህሎት እንደጨበጡ አረጋገጡ |
| **SERVICE USERS' CORNER** | | **የተጠቃሚዎች ጥግ** |
| Street boy determines to win life's struggle | 19 | የጐዳናው ታዳጊ ህይወትን ለማሸነፍ ቆርጧል |


## News

### Education Bureau grants books to JeCCDO

The Hawassa City Education Bureau provided JeCCDO with 1,800 books for Alternative Basic Child Education and Functional Adult Literacy programs in April, 2011.

The provided materials will be used for accessing education service for Orphan and Vulnerable Children (OVC) and other children who cannot join formal education as well as illiterate OVC guardians and adults of the target community.

## ዜና

### የትምህርት ቢሮው ለኢሕማልድ መጻሕፍት ለገሠ

በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መ የሀዋሣ ከተማ ትምህርት ቢሮ በሚያዝያ፣ 2003 ዓ.ም 1,800 መጻሕፍት ለኢሕማልድ ለገሠ:: የተገለሡት መጻህፍት ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትና ለተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት መርሐ-ግብሮች የተዘጋጁ ናቸው::

የመጻሕፍቱ ተጠቃሚዎችም በዋነኛነት ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች መደበኛ ትምህርት መከታተል ያልቻሉ ሕጻናት እና አሳዳጊዎቻቸው ይሆናሉ::



Partial view of the books donated

የተበረከቱት መጻሕፍት በከፊል

Submit comments and articles to: Jerusalem Children and Community Development Organization P. O. Box 41742 E-mail: jeccdo@ethionet.et Addis Ababa, Ethiopia
አስተያየት ወይም ጽሁፍ ቢኖርዎ፡ ኢየሩሳሌም የሕጻናትና ማኅበረሰብ ልማት ድርጅት የመ.ሣ.ቁ. 41742 ኢ-ሜይል፡ jeccdo@ethionet.et አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## JeCCDO signs agreement for water supply, sanitation, hygiene promotion project

JeCCDO entered a project agreement with WaterAid Ethiopia on Water Supply, Sanitation and Hygiene Promotion (WaSH) for disadvantaged groups with a total budget of birr 6,066,755.00, out of which 459,813.00 is a contribution from the community.

The project, which was signed on 13 April 2011, has the objective of contributing towards the improvement of the health condition of the target communities, mainly women and children, through improved WaSH services. The target communities are Ura Kebele residents, children in five primary schools and the Ura Kidane Mihret Church community in Bahir Dar City Administration, Ethiopia.

The project, which runs from April 2011 – March 2015, is expected to benefit more than 40,938 people. Specific activities of the intervention include providing potable water; introducing rainwater harvesting scheme; availing sanitation facilities; hygiene promotion; capacity development; networking and promotion; and documentation, learning and sharing.

## የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጂን ፕሮጀክት ስምምነት ተፈረመ

ኢሕማልድ በ6,066,755.00 ብር በጀት የሚተገበር የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጂን ፕሮጀክት ከወተር ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በሚያዝያ 5 ቀን 2003 ዓ.ም ተፈራረመ። ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥ 459,813.00 ብር ከማኅበረሰቡ የሚዋጣ ይሆናል። የፕሮጀክቱ ዓላማም የተሻሻለ የውኃ፣ የግልና የአካባቢ ንፅህና አገልግሎት በማቅረብ ፕሮጀክቱ ትኩረት ያደረገበትን ኅብረተሰብ የጤና ሁኔታ ማሻሻል ነው። ፕሮጀክቱ ትኩረት ያደረገው በአማራ ብሔራዊ ክልል ባህር ዳር ከተማ የሚገኙ የኡራ ቀበሌ ነዋሪዎችን፣ የአምስት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችንና የኡራ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን ማኅበረሰብን ነው።

ከሚያዝያ 2003 ዓ.ም እስከ መጋቢት 2007 ዓ.ም የሚቆየው ይኸው ፕሮጀክት ከ40,938 በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ አብዛኞቹ ሴቶችና ሕጻናት ናቸው።

በፕሮጀክቱ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የንፁህ ውኃና የመፀዳጃ አገልግሎቶችን ማሻሻል፣ የዝናብ ውኃ በመሰብሰብና በማጠራቀም ለእርሻ የሚውልበትን ዘዴ ለኅብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣ የሥነ-ንፅህና አጠባበቅ ዘዴን ለኅብረተሰቡ ማስተማር፣ የአቅም ልማት፣ ጥምረት፣ ቅስቀሳ፣ መረጃ አያያዝ፣ መማማርና መልካም ተሞክሮዎችን መለዋወጥ ይገኙበታል።



*Left to right: Ms. Sarina Prabasi (Country Representative of WaterAid in Ethiopia and Chair of WaSH Ethiopia Movement) and Mr. Tesfaye Yihune (Acting Executive Director of JeCCDO)*

*ከግራ ወደ ቀኝ፡ ሚስ ሳሪና ፕራባሲ (በኢትዮጵያ የወተር ኤይድ ተወካይ እና የኢትዮጵያ የውኃ፣ ሳኒቴሽን እና ሀይጂን ንቅናቄ ሰብሳቢ) እና አቶ ተስፋዬ ይሁኔ (የኢሕማልድ ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስፈጻሚ)*

## JeCCDO participates in Go Green Afrique Africa International Fair

JeCCDO participated in the first Go Green Afrique Africa International Fair which was organized by Initiative Africa from 23 – 26 June 2011 at the Addis Ababa Exhibition Center.

The primary objective of the event was to bring to the attention of the public, practices and products that cause less harm to the environment and encourage governmental organizations, business and Civil Society Organizations to operate in a way that reduces negative impacts on the environment.

During the fair, which accommodated over 60 exhibitors, JeCCDO disseminated information and shared its experience on maintaining healthy environment especially through urban agriculture and community managed disaster risk reduction activities.

The event was also a good opportunity for JeCCDO to promote and get feedback on its services to the community.

## ኢሕማልድ ዓለም-አቀፍ ዐውደ-ርዕይ ላይ ተሳተፈ

ኢሕማልድ ኢኒሼቲቭ አፍሪካ ባዘጋጀውና ከሰኔ 16 - 19/2003 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል በተካሄደው የመጀመሪያው “ወደ አረንጓዴ አፍሪካ ዓለም-አቀፍ ዐውደ-ርዕይ” ላይ ተሳተፈ። የዐውደ-ርዕይው ዋና ዓላማም አካባቢን የማይጐዱ ተሞክሮዎችንና ቁሳቁሶችን ማስተዋወቅና መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትንና የንግዱን ማኅበረሰብ በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማያስከትል መልኩ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ለማበረታታት ነው።

ከስልሣ በላይ ድርጅቶችና ግለሰቦች የተሳተፉበት ይህ ዐውደ-ርዕይ በበርካታ ሰዎች የተጐበኘ ሲሆን ኢሕማልድ ጤናማ አካባቢን በመጠበቅ ዙሪያ በተለይም የከተማ ግብርናና የማኅበረሰብ-መር የአደጋ ተጋላጭነት ቅነሳ ላይ ያለውን ልምድ አካፍሏል።

ዝግጅቱ ለኢሕማልድ የልማት ተግባራቶቹን ለማስተዋወቅና ለማኅበረሰቡ በሚሰጠው ግልጋሎት ላይ ግብረ-መልስ ለማግኘት ጥሩ መድረክ ፈጥሯል።



*H.E. Mr. Assefa Kessito, Special Advisor to the Presdient, visiting JeCCDO’s exhibition booth*

*የተከበሩ አቶ አሰፋ ከሲቶ፣ የፕሬዚዳንቱ ልዩ አማካሪ የኢሕማልድን ዐውደ-ርዕይ ሲጐበኙ*

## Project to benefit more than 16,000 students

JeCCDO, in collaboration with American Jewish World Service, launched a school girls' empowerment project expected to reach more than 16,000 students in Bishofftu town. The goal of the project is to make the school environment conducive for girl students in order to increase their participation and improve their academic performance. The launching event took place on Thursday, 14 April 2011 at JeCCDO-Debre Zeit Training Center in the presence of representatives from the Bishofftu Town Administration Education Office, Women and Children's Affairs Office as well as teachers and students from 17 schools included in the project.

On the occasion, Ms. Zewidnesh Assefa, Vice Head of Bishofftu Town Education Office, underlined, among others, the need for all stakeholders to work hard towards the sustainable end of the project. Ms. Zewdnesh further indicated that the Office is always ready to cooperate with JeCCDO in every way.

The project was successfully piloted from 2008–2010 on Adea Model High School and benefited approximately 2,500 students. The main project now is scaling up to replicate results achieved during the pilot to other 16 schools in the town through networking.

At the end of the event, an Executive Committee of seven students and a Monitoring and Evaluation Committee of three members (consisting of two students and a teacher) were formed for the network. In addition, a teacher was assigned as a coordinator.

A total of 125 people attended the event.

## ከ16,000 በላይ ተማሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ተከፈተ

በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኙ ከ16,000 በላይ ተማሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ሚያዚያ 6 ቀን 2003 ዓ.ም በከተማው አስተዳደር በሚገኘው የኢሕማልድ ሥልጠና ማዕከል ተከፈተ። ኢሕማልድ ከአሜሪካን ጁዊሽ ወርልድ ሰርቪስ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የሚያካሄደው ይህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማው ት/ቤትን ለሴቶች ተማሪዎች ምቹ በማድረግ ተሳትፎአቸውንና የትምህርት ውጤታቸውን ማሻሻል ነው።

ወ/ሮ ዘውድነሽ አሰፋ፣ የቢሾፍቱ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ም/ኃላፊ በመክፈቻ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ እንዳስገነዘቡት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለኘሮጀክቱ ዘለቄታዊ ውጤት ሊረባረቡ ይገባል። ወ/ሮ ዘውድነሽ አያይዘውም ጽ/ቤታቸው ምንጊዜም ከኢሕማልድ ጋር በልማት ለመተባበር ዝግጁ እንደሆነ አረጋግጠዋል።

ከ2000ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት ሦስት ዓመታት በቢሾፍቱ ከተማ በሚገኘው የአድአ ሞዴል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ የተካሄደው የመነሻ ፕሮጀክት 2,500 የሚጠጉ የት/ቤቱን ተማሪዎች ተጠቃሚ ከማድረጉም በላይ አመርቂ ውጤት ተገኝቶበታል። በዕለቱ የተከፈተው ዋናው ፕሮጀክትም በአድአ ሞዴል ት/ቤት ላይ የተካሄደውን የሙከራ ፕሮጀክት መሠረት በማድረግ በቢሾፍቱ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ሌሎች 16 ት/ቤቶች ላይ በጥምረት ለመሥራት የታቀደ ነው።

በፕሮጀክቱ መክፈቻ መርሐ-ግብር መጨረሻም ሰባት ተማሪ አባላትን የያዘ የጥምረቱ የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴና ሦስት አባላት ያሉት አንድ የቁጥጥርና ግምገማ ኰሚቴ (ከተማሪዎችና መምህራን የተውጣጣ) ተቋቁመዋል። በተጨማሪም አንዲት መምህርት በአስተባባሪነት ተመርጠዋል።

በዕለቱ ዝግጅት ላይ ከከተማው አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤትና የሴቶች፣ ወጣቶችና ሕጻናት ጽ/ቤት እንዲሁም የ17 ት/ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች ተወካዮች በአጠቃላይ 125 ተሳታፊዎች ተገኝተዋል።



*Partial view of participants*

*የዐውደ-ጥናቱ ተሣታፊዎች በከፊል*

## JeCCDO signs memorandum of understanding with Amhara Cluster Edukans Partners

JeCCDO signed a Memorandum of Understanding (MoU) with three member organizations of the Amhara Cluster Edukans Partners that are working on education in the Amhara National Regional State. These partner organizations are Facilitator for Change, Nurture Education and Development and Wabe Children's Aid and Training.

The MoU, which was signed on 19 May 2011 at the Development Expertise Centre- the local front line office for Edukans Foundation, the Netherlands-will be applicable for the whole project period (2011 – 2015). The aim of the MoU is to strengthen the already established Cluster for a more meaningful coordination and efficient utilization of efforts and resources in the region and to ultimately accomplish the objectives of the selected thematic area, Education for all!

The Amhara Cluster Edukans Partners have been working on education projects in favor of underprivileged out-of-school children for more than a decade with the financial support of the Edukans Foundation.

## ኢሕማልድ የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ

ኢሕማልድ በአማራ የኢዱካንስ አጋሮች ጥምረት ከሆኑና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በትምህርት ዙሪያ ከሚሠሩ ሌሎች ሦስት ድርጅቶች ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ። ድርጅቶቹም ፋሲሊቴተር ፎር ቼንጅ፣ ነርቸር ኢዱኬሽን ኤንድ ዴቨሎፕመንት እና ዋቢ የሕጻናት መርጃና ማሠልጠኛ ናቸው።

በግንቦት 11 ቀን 2003 ዓ.ም የተፈረመው መግባቢያ ሰነድ ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ የሚፀና ሲሆን ጥምረቱን የበለጠ ለማጠናከር፣ ሀብትንና አቅምን በብቃት ለመጠቀም እና "ትምህርት ለሁሉም!" የተሰኘውን መርህ በተሳካ ሁኔታ ወደተግባር ለመተርጐም በቅንጅት እንዲሠሩ ለማስቻል የታለመ ነው።

በአማራ የኢዱካንስ አጋሮች ከኢዱካንስ ፋውንዴሽን በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በአማራ ብሔራዊ ክልል ከአሥር ዓመታት በላይ በተለያዩ የትምህርት ነክ ፕሮጀክቶች ላይ በመሳተፍ በተለይም ዕድሉን ላላገኙ ሕጻናት የትምህርት ዕድል በመፍጠር በርካታ ተግባራትን ሲያከናውኑ ቆይተዋል።



*The signing ceremony*

የፊርማው ሥነ-ሥርዓት

## Community based organizations takeover projects of nearly 9 million birr

JeCCDO-Hawassa CDPO officially handed over an Integrated Urban Community Based Child Care (IUCBCC) project, which was implemented for the last 7 years and worth of 9 million birr, to Beminet Enisira and Misrak Chora Community Development Associations (CDAs) on 19 June 2011 in Hawassa. More than 800 people drawn from governmental and nongovernmental organizations and residents of three project Kebeles targeted by the project took part in the event.

Mr. Mulugeta Gerbru, Executive Director of JeCCDO, in his key note speech informed participants that JeCCDO is working with 128 similar Community Based Organizations in 15 parts of the country. The support involves strengthening the capacities of these institutions and handing over projects to the vibrant organizations to sustain the initiatives. He also called upon all concerned governmental and nongovernmental organizations in attendance to extend their support to these dynamic community organizations as they are the pillars of today's development paradigm. Ms. Zewditu Gebre Tsadik, Misrak Sub-city Administrator, on her part, remarked that JeCCDO has always been commendable and confirmed that the Sub-city will support the graduating CDAs in every way possible.

Finally, JeCCDO handed over office equipment and working capital. Project handing over agreements were also signed with representatives of the concerned CDAs. At the same time, two educational billboards on environment and waste management, undertaken by JeCCDO's partner, Hawassa Green Image with the financial support of JeCCDO and the Finland Embassy, were also inaugurated. In all, the event was decorated with the magnificent musical performance of an Ethiopian Idol show finalist of the year, Eyerusalm Reproductive Health Association, which was established and being capacitated by JeCCDO.



*Mr. Mulugeta Gebru, JeCCDO's Executive Director, handing over the project*

*አቶ ሙሉጌታ ገብሩ፣ የኢሕማልድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ኘሮጀክቱን ሲያስረክቡ*

## የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት 9 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ፕሮጀክት ከኢሕማልድ ተረከቡ

በኢሕማልድ የሀዋሳ ማ/ል/ፕ/ጽ/ቤት ግምቱ 9 ሚሊዮን ብር የሚጠጋና ላለፉት 7 ዓመታት ሲተገበረው የቆየውን የተቀናጀ የከተማ ማኅበረሰብን መሰረት ያደረገ የሕጻናት ድጋፍና ክብካቤ ፕሮግራም ሰኔ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ለሁለት የማኅበረሰብ ምስርት ተቋማት አስረከበ፡፡ በርክክቡ ወቅትም ከ800 በላይ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ እንዲሁም የማኅበረሰብ ምስርት ተቋማት ተወካዮችና የፕሮጀክት ማኅበረሰቡ አባላት ተገኝተዋል፡፡

አቶ ሙሉጌታ ገብሩ፣ የኢሕማልድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመክፈቻ ንግግራቸው የድርጅቱን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች፣ የትግበራ አካባቢዎችና መሰል የፕሮጀክት ርክክብ ሂደት ልምድ አውስተው በስብሰባው የተገኙትን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በዕለቱ ፕሮጀክቱን ለሚረከቡት ተቋማት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ወ/ሮ ዘውዲቱ ገ/ፃዲቅ የምስራቅና ባህል አዳራሽ ክፍለ-ከተማ ዋና ሥራ አስኪያጅ በበኩላቸው የኢሕማልድ የሥራ እንቅስቃሴ በተጨባጭ የሚታይ መሆኑን በመግለፅ ለማኅበረሰብ ምስርት ተቋማቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ቃል ገብተዋል፡፡

በመጨረሻም የተለያዩ የጽ/ቤት መሣሪያዎችና የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም የፕሮጀክት ሰነድ ርክክብ የተካሄደ ሲሆን የኢሕማልድ አጋር ድርጅት የሆነው የሀዋሳ ግሪን ኢሜጅም በኢሕማልድ-ፊንላንድ ኤምባሲ የገንዘብ ድጋፍ በከተማዋ ያስተከላቸውን በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ትምህርታዊ የሆኑ ሁለት ሰሌዳዎች አስመርቋል፡፡

የርክክቡ ወቅት በኢሕማልድ ተቋቁሞ በሥነ-ተዋልዶ ጤና ዓይነተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ በሚገኘውና በአሁኑ ወቅትም በኢትዮጵያ አይዶል ሾው የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪ በሆነው የኢየሩሳሌም የውዝዋዜ ቡድን ደምቆ ውሏል፡፡

## Comic Relief's Chief Executive Officer visits JeCCDO

Comic Relief's Chief Executive Officer, Mr. Kevin Cahill, along with members of the Trusty and other affiliated members from UK, visited JeCCDO's programs in Bishofftu on 1 June 2011.

The group heard briefings from Community Based Organizations (CBOs) and various groups in a plenary and separately at the start of the visit.

Practical visits to the project communities including persons with HIV, beneficiaries of guardian economic empowerment and communal facilities constructed were also part of the program. In order to get a comparative view, the group also visited non-beneficiary slum dwellers. JeCCDO's urban agriculture demonstration site and the Training Centre under construction were also sites visited. In this connection, the visitors had a chance to interact with CBOs leaders who were in attendance of training and review meeting in the centre. Finally, the group planted indigenous tree seedlings in the designated area of the centre and forwarded their positive impressions towards JeCCDO's work.

Upon his return, Mr. Kevin Cahill, sent a letter of gratitude to JeCCDO in awe of JeCCDO's organizing an inspiring visit. He remarked, "Our guests were really impressed by the work they saw and our feedback has been excellent. It is a unique opportunity for us to bring the work alive and to make sure Comic Relief's influential friends continue to be committed to us into the future."

## የኮሚክ ሪሊፍ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ኢሕማልድን ጎበኙ

የኮሚክ ሪሊፍ ዋና ሥራ አስፈፃሚን ጨምሮ የድርጅቱን ባለአደራ ቦርድ አባላት፣ የፊልም ተዋናይ እንዲሁም የቴሌቪዥን ባለሙያዎችን ያካተተ የጎብኚዎች ቡድን በቢሾፍቱ ከተማ የሚከናወኑትን የኢሕማልድ የሥራ እንቅስቃሴዎች ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጎበኙ፡፡ በጉብኝቱ ወቅትም የተለያዩ የማኅበረሰብ ምስርት ተቋማት ተወካዮች ተገኝተው አጭር ሪፖርቶችን አሰምተዋል፡፡ በመቀጠልም ቡድኑ ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ሕጻናት አሳዳጊ ቤተሰቦችን፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖችንና የጋራ መጠቀሚያ ግንባታዎችን የጎበኘ ሲሆን ለንፅፅር እንዲመችም በፕሮጀክት ያልታቀፉ ኑሮአቸው እጅግ ዝቅተኛ የሆነ ቤተሰቦችን የአኗኗር ሁኔታ ተመልክቷል፡፡

በተጨማሪም እንግዶቹ የከተማ ግብርና ሠርቶ ማሳያንና በግንባታ ላይ ያለውን የሥልጠና ማዕከል የጎበኙ ሲሆን በተጓዳኝም በስልጠና ላይ የሚገኙ የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት አመራር አካሎችን አግኝተው ተወያይተዋል፡፡

በመጨረሻም ጎብኚዎቹ ያደረባቸውን ስሜት የገለጹ ሲሆን ለማስታወሻም አገር-በቀል ዛፎችን በተጠቀሰው ማዕከል ቅጥር ግቢ ውስጥ ተክለዋል፡፡

የኮሚክ ሪሊፍ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ሚስተር ኬቪን ካሂል ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ በኢሕማልድ ለተሠናዳው አስደሳች የጉብኝት ወቅት የምስጋና ደብዳቤ ልከዋል፡፡ በደብዳቤውም "እንግዶቻችን ባዩት ነገር በጣም በመደነቀ እጅግ በጣም ጥሩ ግብረ-መልስ ሰጥተውናል፡፡ ዝግጅቱ የተሠሩትን ሥራዎች በተጨባጭ ለማሳየት እና ዋና ዋና ረዳቶቻችን ለወደፊቱም ከጐናችን እንዳይለዩን ለማረጋገጥ ልዩ አጋጣሚ ፈጥሮልናል፡፡" በሚል ሀሳባቸውን አስፍረዋል፡፡



*Guests interacting with JeCCDO's staff and CBO members during a coffee ceremony*

*የኮሚክ ሪሊፍ እንግዶች ከኢሕማልድ ሠራተኞች እና ከማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት አባላት ጋር ቡና እየጠጡ ሲወያዩ*

## Grant award to reach children, guardians at risk of HIV and AIDS

JeCCDO awarded five community based organizations with a total of birr 875,000.00 grant to support orphan and vulnerable children (OVC) and guardians, who are at risk of HIV and AIDS. The project signing ceremony was held at JeCCDO-Debre Zeit CDPO on 17 June 2011.

Firelight Foundation, a US based humanitarian organization, funded this project and sub grantee Community Based Organizations (CBOs) were recruited from Nefas Mewcha (South Gondar), Bahir Dar, Bishofftu, Adama and Hawassa cities.

The project, which lasts from April 2011 – December 2011, will benefit 500 OVC, 25-30 OVY, and more than 100 guardians. It also aims at capacitating CBOs through experience sharing, income generation, project planning, networking and linkage and reporting among others.

## ለኤች አይ ቪ እና ኤድስ የተጋለጡ ሕጻናትንና አሳዳጊዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገንዘብ ድጋፍ ተደረገ

ኢሕማልድ ለአምስት የማኀበረሰብ ምሥርት ተቋማት የ875,000.00 ብር ድጋፍ አደረገ። ሰኔ 10 ቀን፣ 2003 ዓ.ም በኢሕማልድ የደብረ ዘይት ማ/ል/ፐ/ጽ/ቤት የተካሄደው ይኸው የፕሮጀክት ስምምነት በተለይ ለኤች አይ ቪ እና ኤድስ ተጋላጭ የሆኑ ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ሕጻናትንና አሳዳጊዎቻቸውን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው።

መሠረቱን በአሜሪካ ካደረገው ፋየር ላይት ፋውንዴሽን በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የሚካሄደው ይኸው ፕሮጀክት በነፋስ መውጫ (ደቡብ ጐንደር)፣ ባህር ዳር፣ ቢሾፍቱ፣ አዳማ እና ሀዋሣ ከተሞች ተግባራዊ ይሆናል።

ከሚያዝያ 2003 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 2004 ዓ.ም የሚቆየው ይህ ፕሮጀክት 500 ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ሕጻናት፣ ከ25-30 ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ወጣቶች እና ከ100 በላይ አሳዳጊዎቻቸውን ተጠቃሚ ያደርጋል። በተጨማሪም ፕሮጀክቱ በልምድ ልውውጥ፣ በገቢ ማስገኛ፣ በፕሮጀክት ዕቅድ፣ ጥምረት፣ ሪፖርት አዘገጃጀትና በመሳሰሉ ጉዳዮች አማካኝነት የተቋማቱን አቅም የማጐልበት ተግባር ያከናውናል።



*The signing ceremony*

*የፊርማው ሥነ-ሥርዓት*

## Association supports orphan, vulnerable children

The Kebele 01 & 03 Residents Enat Guada Cluster Level Association (CLA), in Debre Birhan Town, provided support of educational materials to five Orphan and Vulnerable Children (OVC). This was made during the six CLAs' joint quarterly meeting on 20 March 2011.

During the event, Mr. Negesse Negash, Kebele 01 Administrator, said "Such kinds of exercises guaranteed the realization of the 5 years government Growth and Transformation Plan." He further said "JeCCDO has also shown its effort in supporting and empowering women to move aggressively against poverty."

The CLA was formed from 9 Self Help Groups (SHGs) 6 months ago with the initiation of JeCCDO. Enat Guada, within its short life span, has conducted considerable efforts for member SHGs. It has identified weak SHGs and problems faced by these groups, sought solutions and subsequently strengthened the SHGs. It has also secured office from Kebele 01 Administration. In addition, the CLA has obtained 15,000.00 birr from JeCCDO to help out loan disbursement in the SHGs in order to bring SHGs into income generating activities. Furthermore, the CLA has started mobilizing the SHGs' members to clean their surroundings.

## ማኅበሩ ወላጆቻቸውን ላጡና ለችግር ለተጋለጡ ሕጻናት ድጋፍ አደረገ

በደብረ ብርሃን ከተማ የሚገኘው የቀበሌ 01 እና 03 ነዋሪዎች እናት ጓዳ የአጥቢያ ክልል ማኅበር ወላጆቻቸውን ላጡና ለችግር ለተጋለጡ አምስት ሕጻናት የትምህርት መሣሪያዎች ድጋፍ አደረገ። ድጋፉ የተደረገው የአጥቢያ ክልል ማኅበራት የሩብ ዓመት የጋራ ስብሰባቸውን ባካሄዱበት መጋቢት 11 ቀን 2003 ዓ.ም ነበር።

አቶ ነገሠ ነጋሽ፣ በከተማው የቀበሌ 01 አስተዳዳሪ በዝግጅቱ ወቅት እንዳሉት "እንዲህ ዓይነት እንቅስቃሴዎች የመንግሥት የአምስቱ ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዕውን እንደሚሆን ማረጋገጫዎች ናቸው።" አቶ ነገሠ አያይዘውም "ኢሕማልድ ሴቶች ድህነትን እንዲዋጉ በመደገፍና በማብቃት በኩል እያደረገ ያለውን ጥረት በተጨባጭ አሳይቷል" ሲሉ ገልጸዋል።

የቀበሌ 01 እና 03 ነዋሪዎች እናት ጓዳ አጥቢያ ክልል ማኅበር ከስድስት ወራት በፊት በኢሕማልድ አማካኝነት ከዘጠኝ ራስ አገዝ ቡድኖች ጥምረት የተቋቋመ ነው። እስከ አሁን ማኅበሩ ለአባል ቡድኖቹ በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል። ከነዚህም መካከል ደካማ ራስ አገዝ ቡድኖችን በመለየትና ያለባቸውን ችግሮች አንጥሮ በማውጣት ለችግሮቻቸው መፍትሄ በማበጀት ቡድኖቹን ለማጠናከር ጥረት አድርጓል። በተጨማሪም ማኅበሩ የሥራ ማስኬጃ የሚሆነው ጽ/ቤት ከቀበሌ 01 አስተዳደር የተበረከተለት ሲሆን በሥሩ ለሚገኙ የራስ አገዝ ቡድኖች የብድር አገልግሎት በመስጠት በገቢ ማስገኛ ሥራ ውስጥ እንዲሳተፉ ለማድረግ ከኢሕማልድ የ15,000.00 ብር ድጋፍ አግኝቷል። በሌላ በኩል ማኅበሩ የራስ አገዝ ቡድኖቹ አባላት የመኖሪያ አካባቢያቸውን ንፅህና በመጠበቅ በኩል ንቁ ተሣታፊ እንዲሆኑ የማስተባበር ሥራ በመሥራት ላይ ይገኛል።



*Some of the children attended the event* — *ዝግጅቱን የተካፈሉ ሕጻናት በከፊል*

## Society wins the National Hygiene and Sanitation award

Woubet Compost Production and Town Cleaning Cooperatives Society (WCPTCCS), one of the implementing partners of JeCCDO in Debre Birhan, won the National Sanitation and Hygiene Award on the 3rd National Sanitation and Hygiene Festival which was organized by the Ministry of Health and the WaSH Ethiopia Movement in Hawassa from 31 May to 2 June 2011. One of the objectives of the event was to appreciate and celebrate efforts and achievements in the sanitation and hygiene sector. JeCCDO nominated WCPTCCS to the competition as the best performing organization among its partner community based organizations involved in its health and sanitation related projects.

WCPTCCS was established in Debre Birhan town in 19 March 2009 with the intention of solving the poor hygiene and sanitation system of the town in a sustainable manner. JeCCDO identified WCPTCCS as an implementing partner organization in 2010. Since then, JeCCDO has capacitated the Society through the provision of agricultural tools and trainings such as compost and seed bed preparation; strategic planning and management; community and resource mobilization; project designing; and report writing. In addition, JeCCDO has arranged different experience sharing opportunities for WCPTCCS in different regions.

## ማኅበሩ አገር-አቀፍ የሥነ-ንፅህና ሽልማት አሸነፈ

በደብረ ብርሃን ከተማ ከኢሕማልድ አጋር የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው ውብት ኮምፖስት ማምረትና የከተማ ፅዳት ኅብረት ሥራ ማኅበር ለሦስተኛ ጊዜ በአገር-አቀፍ ደረጃ የተካሄደው የሥነ-ንፅህና ሽልማት አሸናፊ ሆነ። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሀይጂን ንቅናቄ በጋራ ያዘጋጁትና ከግንቦት 23 - 25/2003 ዓ.ም በሀዋሣ ከተማ የተካሄደው ሦስተኛው አገር-አቀፍ የሥነ-ንፅህና በዓል አንዱ ዓላማም በሥነ-ንፅህና ዘርፍ የተደረጉ ጥረቶችንና የተገኙ ውጤቶችን ለማሰብና ለማበረታታት ነበር።

ኢሕማልድም ከአጋር የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማቱ መካከል በሥነ-ንፅህና ዘርፍ የተሻለ እየተንቀሳቀሰ ነው ብሎ ያመነበትን ውብት ኮምፖስት ማምረትና የከተማ ፅዳት ኅብረት ሥራ ማኅበርን በዝግጅቱ ላይ ለተደረገው ውድድር እጩ አድርጐ አቅርቧል።

ማኅበሩ በመጋቢት፣ 2001 ዓ.ም በደብረ ብርሃን ከተማ የነበረውን የግልና የአካባቢ ንፅህና ችግር ለዘለቄታው ለመቅረፍ ታልሞ የተቋቋመ ነው። ኢሕማልድ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ከማኅበሩ ጋር በአጋርነት መሥራት የጀመረ ሲሆን በተያያዘም የተለያዩ የገንዘብ የቁሳቁስና የሥልጠና ድጋፎችን በመስጠት እገዛ አድርጐለታል። በተጨማሪም ኢሕማልድ ማኅበሩ በተለያዩ ክልሎች በመሄድ ከመሠል ተቋማት ጋር የልምድ ልውውጥ እንዲያደርግ ሁኔታዎችን አመቻችቶለታል።



*WCPTCCS members on duty*

*የውበት ኮምፖስት ማምረትና የከተማ ፅዳት ኅብረት ሥራ ማኅበር አባላት በሥራ ገበታቸው ላይ*

# TRAINING AND WORKSHOP

## Project review, familiarization sessions take place

A project review meeting and familiarization workshop on JeCCDO-Sida project was conducted in two rounds from 31 May - 1 June 2011 and from 16 - 17 June 2011 at JeCCDO's Training Center, Bishofftu.

One objective of the events was reviewing the success, challenges and lessons learned from the JeCCDO-Sida project in the year 2010. Among the major track records identified during the review meeting were the profitability of small scale businesses that Orphan and Vulnerable Children guardians are engaged in and the effectiveness and impact of the project specifically in its design, implementation, monitoring and evaluation, and sustainability. Besides, the meetings agreed upon the concrete changes observed among Community Based Organizations (CBOs) in reporting, documentation of best practices, resource mobilization as well as financial and administration activities. The events also aimed at familiarizing the CBOs on the 2011 – 2013 JeCCDO-Sida project, which is mainly attributed to its result based management approach.

Seventy three executive members drawn from 36 CBOs took part in the occasions.

# ሥልጠናና ዐውደ-ጥናት

## የፕሮጀክት ትግበራ፣ ውጤትና ማስተዋወቂያ ዐውደ-ጥናቶች ተካሄዱ

የኢሕማልድ-ስዊድን ዓለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት ፕሮጀክት ትግበራ፣ ውጤትና ማስተዋወቂያ ዐውደ-ጥናቶች በሁለት ዙር (ከግንቦት 23 - 24 እና ከሰኔ 9 - 10/2003 ዓ.ም) በቢሾፍቱ የኢሕማልድ የሥልጠና ማዕከል ተካሄዱ።

ከዐውደ-ጥናቶቹ ዓላማዎች መካከል አንዱ በ2002 ዓ.ም የተተገበረው የኢሕማልድ-ስዊድን ዓለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት ፕሮጀክት ስኬት፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተቀሰሙ ትምህርቶች ላይ መወያየት ነበር። ከዚህ አንፃር ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ሕጻናት አሳዳጊዎች የተሰማሩባቸው አነስተኛ ንግዶች አዋጪ እንደሆኑ ተጠቅሷል። በተጨማሪም አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ዕቅድ ዝግጅት፣ አተገባበር፣ ክትትል፣ ግምገማና ዘላቂነት ውጤታማ እንደነበረ ተመላክቷል። ሌላው በውይይቱ የተነሳው ጉዳይ በማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማቱ በኩል በሪፖርት አዘገጃጀት፣ መልካም ተሞክሮዎችን በመዘገብ፣ በሀብት አሰባሰብ፣ በሒሣብ አያያዝና በአስተዳደር ሥራዎች በኩል የታየው ጉልህ አዎንታዊ ለውጥ ነበር።

በሌላ በኩል የመርሐ-ግብሮቹ ዓላማ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም በሥራ ላይ የሚውለውን የኢሕማልድ-ስዊድን ዓለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት ፕሮጀክት ለአጋር የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት ማስተዋወቅ ነበር። ይኸው ፕሮጀክት በተለይ ውጤት ተኰር አሠራርን የሚከተል እንደሆነ ተገልጿል።

በዐውደ-ጥናቶቹ ላይ ከ36 የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት የተውጣጡ 73 የተቋማቱ የሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ አባላት ተሳታፊ ሆነዋል።



*The event* / *ዐውደ-ጥናቱ*

## Key stakeholders workshop on Self Help Group Approach

A one day workshop intended to create awareness on the concepts of Self Help Group (SHG), Cluster Level Association (CLA) and Federation among stakeholders was conducted on 4 April 2011 at JeCCDO-Training Center, Bishofftu. The event, which was intended to create a strong linkage among stakeholders, drew a total of 48 people from Bishofftu Town Administration sector offices and SHGs and CLAs in 7 Kebeles of Bishofftu town.

On the occasion, JeCCDO-Debre Zeit Community Development Program Officer, Mr. Ayenew Aysheshim, presented JeCCDO's experience and achievements in SHG Approach. Representatives from the CLAs on their part made presentations on the various stages they have passed through since inception, their activities, achievements, challenges and the support they have obtained from JeCCDO.

Following the presentations, the workshop made a thorough discussion and appreciated JeCCDO for its effort in establishing these institutions and supporting them afterwards. Participants, especially those representing government sector offices, promised to take on the mantle of supporting and thereby ensuring success and sustainability of the SHGs, CLAs and Federation.



*A CLA representative presenting*

*የአጥቢያ ክልል ማኅበር ተወካይ ለዐውደ-ጥናቱ ተሣታፊዎች ስለማኅበራቸው ሲያስረዱ*

## በራስ አገዝ ቡድን ላይ ያተኰረ ዐውደ-ጥናት ተካሄደ

በራስ አገዝ ቡድን፣ በአጥቢያ ክልል ማኅበራትና በፌዴሬሽን ፅንሰ-ሀሳቦች ላይ ያተኰረ የአንድ ቀን ዐውደ-ጥናት በቢሾፍቱ የኢሕማልድ ሥልጠና ማዕከል ተካሄደ። መጋቢት 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተካሄደው ይህ ዐውደ-ጥናት በተለይ በባለድርሻ አካላት መካከል ጠንካራ ትስስርን እንደሚፈጥር ታምኖበታል።

በዕለቱ በኢሕማልድ የደብረዘይት ማኅበረሰብ ልማት ኘሮግራም መኰንን አቶ አየነው አይሸሽም ኢሕማልድ በራስ አገዝ ቡድን ዙሪያ ያለውን ልምድና ያስመዘገበውን ውጤት ለዐውደ-ጥናቱ ተሳታፊዎች አካፍለዋል። በተጨማሪም በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኙትና በኢሕማልድ ዕገዛ የተቋቋሙት ሰባቱ የራስ አገዝ ቡድን አጥቢያ ክልል ማኅበራት በተወካዮቻቸው አማካኝነት ቡድኖቹና ማኅበራቱ ከአመሠራረት ጀምሮ ያለፉባቸውን ሂደቶች፣ ያከናወኗቸውን ተግባራት፣ ያስመዘገቧቸውን ውጤቶች፣ ያጋጠሟቸውን ችግሮችና ከኢሕማልድ ያገኙትን ድጋፍ በተመለከተ በዐውደ-ጥናቱ ላይ አስረድተዋል።

በመጨረሻም ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ ኢሕማልድ ቡድኖቹንና ማኅበራቱን በመመሥረትም ሆነ ከምሥረታ በኋላ ያላሰለሰ ድጋፍ በመስጠት እዚህ ማድረሱ የሚያስመሰግነው መሆኑ በተሳታፊዎች ተገልጿል። በተጨማሪም የመንግሥት ሴክተር ጽ/ቤቶች ተወካዮች የሆኑት የዕለቱ ዝግጅት ተሳታፊዎች የራስ አገዝ ቡድኖቹ፣ የአጥቢያ ክልል ማኅበራቱና ፌዴሬሽኑ ውጤታማነታቸውንና ዘላቂነታቸውን ለማረጋገጥ ያላሰለሰ ድጋፍ ለመስጠት ቃል ገብተዋል።

ከቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ሴክተር ጽ/ቤቶች እንዲሁም በከተማዋ ውስጥ ከሚገኙ ሰባት ቀበሌዎች የራስ አገዝ ቡድኖችና የራስ አገዝ ቡድን አጥቢያ ክልል ማኅበራት የተውጣጡ በጠቅላላው 48 ሰዎች በዕለቱ መርሐ-ግብር ተሳታፊ ሆነዋል።

## Workshop emphasizes urban agriculture's contribution to poverty reduction, environment

Workshop participants emphasized on the need to implement and promote urban agriculture to reduce poverty and protect the environment. The workshop, which was organized by JeCCDO, in collaboration with Land and Environmental Protection Office of the Bishofftu Town Administration, focused on the contribution of urban agriculture. The event was conducted on 13 April 2011 at JeCCDO- Training Center, Bishofftu.

## የከተማ ግብርና ለድህነት ቅነሳና ለአካባቢ ጥበቃ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተገለጸ

የከተማ ግብርናን ማስፋፋት በድህነት ቅነሳና በአካባቢ ጥበቃ ላይ የጐላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ኢሕማልድና የቢሾፍቱ ከተማ የመሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት በጋራ ባዘጋጁት በከተማ ግብርና ላይ ባተኰረ ዐውደ-ጥናት ላይ ተጠቆመ።

በቢሾፍቱ ከተማ በሚገኘው የኢሕማልድ ሥልጠና ማዕከል ሚያዝያ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተካሄደው በዚህ ዐውደ-ጥናት ሁለት ጥናታዊ ፅሁፎች

During the event, presentations were made by JeCCDO- Debre Zeit Community Development Program Officer and Bishofftu Town Administration Land and Environmental Protection representative on the topics “Potentials of Urban Agriculture to Poverty Reduction” and “Contribution of Urban Agriculture to the Bishofftu City Environment,” respectively. Participants also had a chance to visit JeCCDO’s urban agriculture demonstration site situated in the CDPO’s compound from which thorough discussions ensued. At the end of the event, the workshop pledged for a joint effort to interpret its decisions into reality.



Participants visiting JeCCDO’s demonstration site

*የዐውደ-ጥናቱ ተሣታፊዎች የኢሕማልድን ሠርቶ-ማሳያ ሲጐበኙ*

In related news, JeCCDO in collaboration with Debre Zeit Agricultural Research Center organized a similar workshop on 29 June 2011 at JeCCDO’s Training Center, Bishofftu.

Mr. Ayenew Aysheshim, JeCCDO-Debre Zeit Community Development Program Officer, presented the achievements, challenges and lessons learned throughout JeCCDO’s Urban Agriculture project in Bishofftu. In addition, Ms. Etsegenet Kiflu from the Research Center, presented the results of a research entitled, “Achievements, challenges and lessons learned on Urban Agriculture in the Bishofftu City and the collaboration for Urban Agriculture Development in the City.” Moreover, seven JeCCDO’s urban agriculture beneficiaries from the seven Kebeles in Bishofftu town explained their achievements to the workshop. The meeting, then, paid a visit to JeCCDO-Debre Zeit CDPO Urban Agriculture demonstration site.

After a thorough discussion, participants, especially representatives of the Research Center, Land and Environmental Protection Office, Micro Trade and Industry Agency and Women’s Affairs Office, promised to support the urban agriculture committees in securing special seeds and animals as well as production and market place for their products or anything in their capacity.

A total of 114 people drawn from all sectors of the Bishofftu Town Administration, Urban Agriculture Committees, CBOs, the Debre Zeit Agricultural Research Center and urban agriculture beneficiaries took part in both workshops.

ማለትም “የከተማ ግብርና ለድህነት ቅነሳና ለአካባቢ ጥበቃ የሚኖረው አስተዋጽኦ” በኢሕማልድ የደብረዘይት ማኅበረሰብ ልማት ኘሮግራም መኰንን አቶ አየነው አይሸሽም እና “የከተማ ግብርና ለቢሾፍቱ ከተማ አካባቢ ጥበቃ የሚኖረው አስተዋጽኦ” በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር የመሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ተወካይ ቀርበው ውይይት ተካሄዷል።

በተጨማሪም የዐውደ-ጥናቱ ተሳታፊዎች በዕለቱ በኢሕማልድ የደብረ ዘይት የማ/ል/ፕ/ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኘውን የከተማ ግብርና ሠርቶ-ማሳያ ጐብኝተዋል። በመጨረሻም ሰፊ ውይይት ከተካሄደ በኂላ ተሳታፊዎቹ በዕለቱ የደረሱባቸውን ስምምነቶች ወደተግባር ለመተርጐም ቃል ገብተዋል።

በተያያዘ ዜና ኢሕማልድ ከደብረ ዘይት የግብርና ምርምር ተቋም ጋር በመተባበር ሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም በከተማው ውስጥ በሚገኘው የኢሕማልድ ሥልጠና ማዕከል ዐውደ-ጥናት አካሄዷል።

በዚሁ ዝግጅት አቶ አየነው አይሸሽም፣ የኢሕማልድ ደብረ ዘይት ማኅበረሰብ ልማት የፕሮግራም መኰንን የኢሕማልድ የከተማ ግብርና ኘሮጀክት ያስመዘገባቸውን ውጤቶች፣ በሥራ ሂደት ያጋጠሙትን ችግሮችና የተቀሰሙ ትምህርቶችን አስረድተዋል። በተጨማሪም የግብርና ምርምር ማዕከሉ በወ/ሮ ዕፀገነት ክፍሉ አማካኝነት “በቢሾፍቱ ከተማ የከተማ ግብርና እንቅስቃሴ የተመዘገቡ ውጤቶች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተቀሰሙ ትምህርቶች እና በከተማው ውስጥ የከተማ ግብርናን ለማስፋፋት ያላቸው ትብብር” የተሰኘ ጥናት አቅርቧል። በከተማው የሚገኙ ሰባት ቀበሌዎች ነዋሪዎች የሆኑ ሰባት የከተማ ግብርና ኘሮጀክት ተጠቃሚዎችም ያገኙትን ጥቅም አብራርተዋል። በመቀጠልም የዐውደ-ጥናቱ ተሳታፊዎች በኢሕማልድ የደብረ ዘይት ማ/ል/ፕ/ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኘውን የከተማ ግብርና ሠርቶ-ማሳያ ጐብኝተዋል።

በመጨረሻም የደብረዘይት የግብርና ምርምር ማዕከል የፕሮጀክቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ለከተማ ግብርና ኰሚቴዎቹ የተለያዩ ምርጥ ዘሮችን በመስጠት እገዛ እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል። በተጨማሪም የከተማ ግብርናን ለማስፋፋት የሚረዱ የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች በማግኘት በኩል የከተማው የመሬትና አካባቢ ጥበቃ ቢሮ እና የከተማው ጥቃቅን ንግድና ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ እንደሚተባበሩ አረጋግጠዋል። የከተማው የሴቶች ጉዳይ ቢሮም በቀጣይነት ኮሚቴዎቹ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን ለመፍታት ዝግጁነቱን ገልጿል።

ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ዝግጅቶች ላይ ከቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ቢሮዎች፣ ከከተማ ግብርና ኰሚቴዎች፣ ከማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት፣ ከደብረዘይት የግብርና ምርምር ማዕከል እና ከከተማ ግብርና ተጠቃሚዎች የተውጣጡ በአጠቃላይ 114 ሰዎች ተሳታፊ ሆነዋል።

## Workshop validates research findings

A research supported by JeCCDO in partnership with the European Union was validated on a one day workshop which was carried out on 9 June 2011 in Karamara Hotel, Dire Dawa. Lecturers in Dire Dawa University carried out the research entitled "Enabling Environment, Working Modalities and Systems of Community Based Organizations (CBOs) in Dire Dawa City." The event was intended to enrich the content of the study from participants' feedback and validate the document.



*The event*

*ዐውደ-ጥናቱ*

During the workshop, presentations on the outcome of the research were made and participants raised questions, and made comments and suggestions on the research. Finally, the meeting agreed that the research was timely and important. The participants also indicated that identifying the CBOs' prevailing problems and their external environment based on research helps distinguish the challenges they face and render the necessary support accordingly. The meeting further indicated that more support is needed to increase their role in the development process.

A total of 51 participants composed of CBOs, NGOs, Kebele Administration and line government offices representatives attended the event.

## የዐውደ-ጥናቱ ተሳታፊዎች ለጥናቱ ውጤት ተቀባይነት ሰጡ

ኢሕማልድ ከአውሮፓ ኅብረት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የተካሄደ ጥናት ሰኔ 2 ቀን 2003 ዓ.ም በድሬ ዳዋ ከተማ ካራማራ ሆቴል በተዘጋጀ የአንድ ቀን ዐውደ-ጥናት ተቀባይነት አገኘ፡፡ "በድሬ ዳዋ ከተማ ያሉ የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት ምቹ ከባቢ ሁኔታዎች፣ አደረጃጀትና የውስጥ አሠራር" የተሰኘው ይህ ጥናት በድሬ ዳዋ ዩኒቨርስቲ መምህራን የተካሄደ ነው፡፡ የዐውደ-ጥናቱ ዓላማ ከተሳታፊዎች በሚነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የጥናቱን ይዘት ለማዳበርና በመጨረሻም ጥናቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማስቻል ነበር፡፡

በዕለቱ የጥናቱ ውጤት የቀረበ ሲሆን በመቀጠልም አስተያየቶች፣ ጥያቄዎችና ማጠናከሪያ ነጥቦች ቀርበው ሰፊ ውይይት ተካሄዷል፡፡ በመጨረሻም የዐውደ-ጥናቱ ተሳታፊዎች ጥናቱ ተገቢ፣ ወቅታዊና አስፈላጊ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡ በተጨማሪም ዋነኛ የልማት አጋዥ የሆኑትን የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት ያሉባቸውን ችግሮችና ከባቢ ሁኔታዎቻቸውን በጥናት መነሻነት ማውጣት ችግሮቻቸውን ቁልጭ አድርጐ ከማሳየቱም በላይ ተገቢ የሆነ ድጋፍ ለመስጠትም ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የዐውደ-ጥናቱ ተሳታፊዎች ተስማምተውበታል፡፡ ተሳታፊዎቹ አያይዘውም ተቋማቱ የበለጠ የልማት አጋዥ እንዲሆኑ ከሁሉም ወገን የተጠናከረ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው አስምረውበታል፡፡

የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት፣ የቀበሌ ጽ/ቤቶችና ሌሎች የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር ሴክተር ጽ/ቤቶች ተወካዮች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች በአጠቃላይ 51 ተሳታፊዎች በዐውደ-ጥናቱ ላይ ተገኝተዋል፡፡

## Workshop on gender sensitive modules

A four day workshop on gender sensitive modules was organized from 4 – 7 May 2011 at JeCCDO's Training Center, Bishoftu. The workshop was aimed at enriching and getting feedback on five gender sensitive modules, which were prepared through the support of JeCCDO/Oxfam Canada project. Besides, the event was intended to develop Community Based Organizations' (CBOs') capacity in facilitating equal participation of men and women in the development process.

## ሥርዓተ-ፆታን ያማከሉ መመሪያዎችን ለማዘጋጀት የምክክር ዐውደ-ጥናት ተካሄደ

ሥርዓተ-ፆታን ያማከሉ አጋዥ መመሪያዎችን (ማንዩአሎችን) ለማሻሻል የምክክር ዐውደ-ጥናት ከሚያዝያ 26-29/2003 ዓ.ም ቢሾፍቱ ከተማ በሚገኘው የኢሕማልድ ሥልጠና ማዕከል ተካሄደ፡፡ የመርሐ-ግብሩ ዓላማም በኢሕማልድ-ኦክስፋም ካናዳ ፕሮጀክት ድጋፍ ከዚህ ቀደም በተዘጋጁ አምስት ሥርዓተ-ፆታን ያማከሉ መመሪያዎች ላይ ግብረ-መልስ በማሰባሰብና በማስተካከል መመሪያዎቹን ብቁ ለማድረግ እንዲቻል ነው፡፡ በተጨማሪም የዝግጅቱ ፋይዳ የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማትን ሴቶችና ወንዶች በልማቱ ላይ እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማመቻቸት እንዲችሉ አቅማቸውን ማሳደግ ነው፡፡

The modules were teemed with Poverty Analysis in the Local Context; Leadership; Group Dynamics and Teamwork; Project Designing and Implementation; and Operational Planning. These modules are expected to enhance the capacity of CBOs to engage in development activities for the benefits of both men and women equally.

At the end of the event, participants reflected that the workshop employed appropriate adult learning methods through participatory approach, locally available training aids, role plays, drama, and group and plenary discussion.

Thirty six executive members (17 women) from 18 CBOs took part in the event.

መመሪያዎቹ ሥርዓተ-ፆታን ያማከለ የድህነት ትንተና፣ አመራር፣ ቡድንና የቡድን መስተጋብር፣ የፕሮጀክት ዑደት እና የዕቅድ ዝግጅት ጭብጦች ላይ ያተኮሩ ሲሆን ተቋማቱ ሁለቱንም ፆታዎች ተጠቃሚ የሚያደርጉ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያበቁ ናቸው። በመርሐ-ግብሩ መጨረሻ ተሳታፊዎቹ እንዳመለከቱት ዐውደ-ጥናቱ አሳታፊ የማስተማር ስልትን፣ በአካባቢ የሚገኙ የትምህርት መርጃዎችን፣ የሚና ጨዋታን፣ ጭውውትን እና የቡድንና የተሳታፊዎች ውይይትን በማካተቱ ተገቢ የሆነ የጐልማሶች ማስተማሪያ ዘዴን የተከተለ ነበር።

በአጠቃላይ ከ18 የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት የተውጣጡ 36 የተቋማቱ የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ አባላት በዐውደ-ጥናቱ የተሳተፉ ሲሆን ከነዚህም መካከል 17 ሴቶች ይገኙበታል።



*Participants discussing on the results of group work*

ተሣታፊዎች በቡድን ሥራ ውጤት ላይ ሲወያዩ

## Child parliament speaker visits the Netherlands

Getahun Wuletaw, 18 and Speaker of Hawassa Children Parliament, visited the Netherlands from 22-29 May 2011. The visit was organized by the Foundation for International Research on Working Children (IREWOC) in cooperation with the International Child Development Initiatives (ICDI). The aim of the program was to bring together seven children engaged in the promotion of children's issues and give them the opportunity to extend their networks, learn from each other and experts, validate their efforts, cross borders and overcome barriers.

During his stay in the Netherlands, Getahun attended a two-day seminar and visited organizations working on the promotion of child wellbeing among others. He also secured 2,500 Euros which will be used to implement a children focused project he has designed. The fund was obtained from ICDI, IREWOC and the Netherlands Youth and Sport Office.

"I'm very proud of my participation to promote the issues of children at the international level. I have learned a lot from experiences of others particularly of their strategies to deal with challenges," said Getahun. According to him, the event has encouraged him to think of preparing another national level project in the future. He extended his sincere gratitude to JeCCDO and other organizations that facilitated his visit.

JeCCDO played a significant role in the establishment of the Hawassa Children Parliament and nominated Getahun for the visit to the Netherlands considering his contribution in the establishment of the Parliament as well as effort to tackle harmful traditional practices that threaten the wellbeing of children.



*Getahun, speaking on the event*

*ጌታሁን በዝግጅቱ ላይ ንግግር ሲያደርግ*

## የሕጻናት ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ኒዘርላንድን ጎበኘ

የሀዋሣ ከተማ ሕጻናት ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የሆነው የ18 ዓመቱ ታዳጊ ጌታሁን ውለታው ከግንቦት 14-21/2003 ዓ.ም ኒዘርላንድን ጎበኘ። ጉብኝቱን ያዘጋጀው ዘ ፋውንዴሽን ፎር ኢንተርናሽናል ሪሰርች ኦን ወርኪንግ ቺልድረን የተባለ ድርጅት ነው። የመርሐ-ግብሩ ዓላማም በተለያዩ የዓለም ክፍል የሚገኙ የሕጻናት ጉዳዮችን የሚያስተዋውቁ ሰባት ሕጻናትን በማገናኘት ጥምረታቸውን እንዲያጠናክሩ፣ እርስ በእርሳቸው እንዲማማሩ፣ ሥራዎቻቸውን እንዲያስተዋውቁና ችግሮቻቸውንም እንዲፈቱ ምቹ መድረክ መፍጠር ነው።

ጌታሁን በኒዘርላንድ ቆይታው የሁለት ቀን ሴሚናር የተካፈለ ሲሆን በሕጻናት ጉዳይ ላይ የሚሠሩ ድርጅቶችንም ጎብኝቷል። በተጨማሪም ለቀረጸው የሕጻናት ተኮር ፕሮጀክት ማስኬጃ የሚውል 60,000.00 ብር የሚጠጋ የገንዘብ ዕርዳታ ለማግኘት ችሏል። ዕርዳታው የተገኘውም ከሁለቱ የጉብኝቱ አዘጋጅ ድርጅቶች እና ከኔዘርላንድ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ነው።

"በዓለም-አቀፍ ዝግጅት ላይ በመገኘት የሕጻናትን ጉዳይ ለማስተዋወቅ በመቻሌ ኩራት ይሰማኛል። የተለያዩ አገራት ያላቸውን ልምድ እና በሥራቸው ላይ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መፍቻ ስልቶች በተመለከተ በርካታ ልምድ ቀስሜያለሁ" ያለው ጌታሁን በዝግጅቱ ያገኘው ልምድ ለወደፊቱ በአገር-አቀፍ ደረጃ የሚካሄድ ትልቅ ፕሮጀክት ለመቅረጽ እንዳነሳሳው አስታውቋል። ኢሕማልድን ጨምሮ ለሌሎች ጉብኝቱን ላመቻቹለት ድርጅቶችም ሁሉ ምስጋናውን አቅርቧል።

ኢሕማልድ በሀዋሣ የሕጻናት ምክር ቤት ምሥረታ ላይ ጉልህ ሚና የነበረው ሲሆን ጌታሁንን ለኒዘርላንዱ ጉብኝት ተሣታፊነት ሊጠቁመው የቻለው ለምክር ቤቱ ምሥረታ ባበረከተው አስተዋጽኦ እና የሕጻናትን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመዋጋት የሚያደርገውን ጥረት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

## Capacity development trainings to partner community based organizations' executives

Capacity development trainings for executive committee members of 50 implementing partner community based organizations of JeCCDO were organized from March – May, 2011. The trainings covered Organizational Development; Fund Raising and Report Writing; Strategic Planning and Management; and Leadership.

The three days trainings, coordinated by the Capacity Development Unit of JeCCDO, were carried out in all the five operational areas of the organization i.e., Bishofftu, Debre Birhan, Bahir Dar, Hawassa and Dire Dawa.

One hundred fifty six participants (52 women), were in attendance of the trainings.



*Participants in Debre Birhan during group discussion*
*በደብረ ብርሃን የተካሄደው ሥልጠና ተሣታፊዎች በቡድን ውይይት ላይ*

## ለአጋር የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት አመራር አካላት የአቅም ልማት ሥልጠናዎች ተሰጡ

የኢሕማልድ አጋር የሆኑ 50 የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የተካፈሉባቸው የአቅም ልማት ሥልጠናዎች ከመጋቢት - ግንቦት 2003 ዓ.ም ተካሄዱ። የሥልጠናዎቹ ይዘትም ድርጅታዊ ዕድገት፤ ሀብት አሰባሰብና ሪፖርት አዘገጃጀት፤ ስልታዊ ዕቅድና ሥራ አመራር አስተዳደር፤ እና አመራር ናቸው።

በኢሕማልድ የአቅም ልማት የሥራ ክፍል የተዘጋጁት እነኚህ ሥልጠናዎች በአምስቱም የድርጅቱ የሥራ ቦታዎች ማለትም በቢሾፍቱ፣ በደብረ ብርሃን፣ በባህር ዳር፣ በሀዋሣ እና በድሬዳዋ ከተሞች በተለያዩ ጊዜያት ለሦስት ለሦስት ቀናት ተካሄደዋል። በመርሐ-ግብሮቹም 156 ሰዎች (52 ሴቶች) ተሣታፊ ሆነዋል።

## Stakeholders' annual review meeting

JeCCDO-Hawassa CDPO conducted an annual review meeting with government bodies, NGOs and Community Based Organizations (CBOs) on 22 March 2011 at Central Hotel, Hawassa. The objectives of the meeting was to brief the concerned stakeholders with the organization's plan, performance, budget utilization and achievements during the 2010 budget year as well as plan for 2011 budget year and general future direction of JeCCDO.

During the ensuing discussions, participants appreciated JeCCDO's transparent working modality and good relationship with different stakeholders as well as its tangible contribution to the government development program. Eighty five people (39 women) participated in the event.



*The workshop*
*ዐውደ-ጥናቱ*

## የባለድርሻ አካላት ዓመታዊ ስብሰባ ተካሄደ

የኢሕማልድ ሀዋሣ ማ/ል/ፕ/ጽ/ቤት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የማኅበረሰብ ምሥርት ተቋማትን ያሳተፈ ዓመታዊ ስብሰባ መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም በሀዋሣ ሴንትራል ሆቴል አካሄደ። የመርሐ-ግብሩ ዓላማ የኢሕማልድን የ2002 የበጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ፣ ክንውን፣ የበጀት አጠቃቀም እንዲሁም የተመዘገቡ ውጤቶችን ለባለድርሻ አካላት ማሳወቅ ሲሆን በተጨማሪም የ2003 የበጀት ዓመት ዕቅዱንና አጠቃላይ የድርጅቱን የወደፊት አቅጣጫም በመጠቆም ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶችን ለማሰባሰብ ነበር።

የዐውደ-ጥናቱ ተሳታፊዎች የኢሕማልድን ግልፅነት የተሞላው የአሠራር ሂደት እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን መልካም የሥራ ግንኙነት እንዲሁም በመንግሥት የልማት ፕሮግራም ትግበራ ላይ ያለውን የጎላ ድርሻ አድንቀዋል።

## Trainees confirm to produce effective stories

“Success Story and News Production Training” participants confirmed their preparedness to produce effective success and news stories for JeCCDO. This was learned from the evaluation of the Training held from 4 – 5 June 2011 at JeCCDO - Training Center, Bishofftu.

The training, attended by 16 program officers, was carried out in the furtherance of the quality of news and success stories produced by JeCCDO.

The results of the training evaluation attested that the training improved participants’ knowledge, skills and preparedness to produce effective success and news stories for JeCCDO.

## ሠልጣኞቹ አመርቂ ታሪኮችን ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው ክህሎት እንደጨበጡ አረጋገጡ

“የስኬት ታሪኮችና የዜና ዝግጅት ሥልጠና” ተሳታፊዎች ሥልጠናው ከተጠናቀቀ በኋላ የሰጡት የግምገማ ውጤት እንዳረጋገጠው በመርሐ-ግብሩ የተሳኩ የስኬትና የዜና ታሪኮችን ለማዘጋጀት የሚያስችላቸው ክህሎትና ዝግጁነትን አዳብረዋል፡፡

ከሰኔ 27 — 28/2003 ዓ.ም በኢሕማልድ የደብረ ዘይት ሥልጠና ማዕከል የተካሄደው ይህ መርሐ-ግብር በኢሕማልድ የሚዘጋጁ የዜናና የስኬት ታሪኮችን ጥራት ለማሳደግ የታለመ ሲሆን ከኢሕማልድ አምስት የማ/ል/ፕ/ጽ/ቤቶች የተውጣጡ 16 የፕሮግራም መኮንኖች ተሳትፈውበታል፡፡



*Partial view of the training event*

የሥልጠናው ሂደት በከፊል

# SERVICE USERS' CORNER

## Street boy determines to win life's struggle

Behailu Teshome, 11, lives in Hawassa city, 270km south of Addis Ababa. His father died some years ago. And his mother, along with his two sisters, lives in deep poverty in Hagereselam town, which is approximately 93km away from Hawassa. Behailu came to Hawassa, in 2010 with his older brother and started to make a living as porter boy on Hawassa streets. But it did not take Behailu long to realize that street life is hazardous and couldn't satisfy his needs at all.

# የተጠቃሚዎች ጥግ

## የጐዳናው ታዳጊ ህይወትን ለማሸነፍ ቆርጧል

የአሥራ አንድ ዓመቱ ታዳጊ በኃይሉ ተሾመ የሀዋሣ ከተማ ነዋሪ ነው። አባቱን ከጥቂት ዓመታት በፊት በሞት ያጣ ሲሆን ምንም መተዳደሪያ የሌላቸው እናቱና ሁለት እህቶቹ ከሀዋሣ ከተማ 93 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምትገኘው ሀገረሰላም ከተማ በችግር ኑሮአቸውን ይገፋሉ። በኃይሉ በ2002 ዓ.ም ነበር ከታላቅ ወንድሙ ጋር ወደ ሀዋሣ ከተማ የመጣው። እናም ሁለቱ ወንድማማቾች በቀን ሠራተኝነት ዕቃ በመሸከም በሚያገኙት ገንዘብ የጐዳና ህይወትን "ሀ" ብለው ጀመሩ። ነገር ግን በኃይሉ ውሎ ሳያድር የተገነዘበው ነገር ቢኖር የጐዳና ህይወት ለአደጋ የተጋለጠና ፈጽሞ ፍላጐቱን ሊያሟላ እንደማይችል ነበር።



*Behailu receiving award for standing first in his class*

*በኃይሉ ከክፍሉ 1ኛ በመውጣቱ ሽልማት ሲቀበል*

In the past, when people asked him why he did not go to school he used to say that he had no money for school fees. Be that as it may, they used to tell him that he was a bad boy for not going to school.

After a while, he was fortunate enough to hear about JeCCDO's Alternative Basic Child Education School and joined it. There, he is provided with education and educational materials for free. His school and work are not affecting one another. In addition, the teachers

በዚያን ወቅት ሰዎች ለምን ወደ ት/ቤት እንደማይሄድ ሲጠይቁት ለዛ የሚከፍለው ገንዘብ እንደሌለው ቢገልጽላቸውም በትምህርት ሰዓት ከት/ቤት ውጪ በመገኘቱ ብቻ መጥፎ ልጅ እንደሆነ ይቆጥሩት ነበር።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም የኢሕማልድን ነጻ የአማራጭ መሠረታዊ ት/ቤት ሲሰማ ትምህርቱን በዚያው ጀመረ። በት/ቤቱ የትምህርት እድል ብቻ ሳይሆን የትምህርት መሣሪያዎችም በነፃ ያገኛል። የሥራ ሰዓቱን በማይሻማበት መልኩ ትምህርቱን መከታተል ከመቻሉም በላይ አስተማሪዎቹ በጣም ጥሩዎችና ችግሩን የሚረዱለት ናቸው። በአንድ

understand him very well. If he misses a lesson, they do not hesitate to compensate. He ranked first from his class in both the first and second semesters and also wants to keep on scoring good grades. And hence, he is not a bad boy anymore!

English is his favorite subject and he likes to play football in the school compound where he feels more secured. After school, he cleans a DStv House for free. Considering his helpfulness, the house owners provided him with a place to put his school materials and stay the nights.

Currently, the school has started a linkage with UK schools that Behailu hopes to make friendship with UK students and thereby learn more about their schooling.

In the future, he wants to be a medical doctor.

ወይም በሌላ ምክንያት ከት/ቤት ቢቀር በሌላ ጊዜ የቀረበትን ያካክሱለታል። በመጀመሪያውና ሁለተኛው መንፈቀ-ትምህርት ከክፍሉ አንደኛ የወጣ ሲሆን ወደፊትም ይህንኑ ደረጃ ይዞ ለመቀጠል ቆርጧል። እናም ዛሬ በኃይሉ ጥሩ ልጅ ነው!

በኃይሉ በጣም የሚወደው የትምህርት ዓይነት እንግሊዝኛ ሲሆን በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ የበለጠ ደህንነት ስለሚሰማው በዚያ ከጓደኞቹ ጋር ኳስ መጫወት ያስደስተዋል።

በኃይሉ ባለው ትርፍ ጊዜ በከተማው ውስጥ የሚገኘን አንድ የዲኤስ ቲቪ ማሳያ ቤት በነፃ ያፀዳ ነበር። በኋላም ጥረቱንና ተባባሪነቱን በማየት የቤቱ ባለቤቶች የትምህርት መሣሪያዎቹን የሚያስቀምጥበትና ሌሊቱንም የሚያሳልፍበት ቦታ ፈቀዱለት።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ት/ቤቱ እንግሊዝ ከሚገኙ ት/ቤቶች ጋር ግንኙነት የጀመረ ሲሆን ይህንን ዕድል በመጠቀም በኃይሉም ከእንግሊዛውያን የዕድሜ እኩዮቹ ጋር ጓደኝነት ለመመሥረት እና ስለትምህርታቸውም ማወቅ ይፈልጋል። የበኃይሉ ምኞት ሀኪም መሆን ነው።

ኢሕማልድ

JeCCDO


## Address

**Central Office**
**JeCCDO**
**P. O. Box 41742**
**Tel. 251-11- 661 10 92**
**Fax: 251-11- 661 10 94**
**E-mail: jeccdo@ethionet.et**
**www.jeccdoethiopia.org**
**Addis Ababa, Ethiopia**

**Community Development Program Offices**

| Bahir Dar | Debre Birhan | Debre Zeit | Dire Dawa | Hawassa |
|---|---|---|---|---|
| P. O. Box 337 | P. O. Box 77 | P. O. Box 45 | P. O. Box 1680 | P. O. Box 1346 |
| Tel. 058-2182221/22 | Tel. 011-6811313 | Tel. 011-4338589 | Tel. 025-1119297 | Tel. 046-210005/6/7 |
| Bahir Dar | Debre Berhan | Debre Zeit | Dire Dawa | Hawassa |


Reha Touch: 091-1209525